# የትግራይ በጠላት እጅ መውደቅ እና በኢትዮጵያ ያስከተለው መዘዝ (ክፍል አንድ)

ከገ/መድህን አርአያ

## መግቢያ ከኢትዮሚድያ ዝግጅት ክፍል



“የህውዜን ጭፍጨፋ ጠንሳሾች ስብሃት እና መለስ ናቸው” - ገ/መድህን አርአያ

የህውዜን ሰማእታት ሀውልት በመቀሌ

(ደሮን ሲያታልልዋት በመጫኛ ጣልዋት ይሉታል ይህ ነው)

ገ/መድህን አርአያ በስልጣን ላይ ስላለው ቡድን ማንነት በተለያዩ ሚድያዎች እያስተማረ ይገኛል። የእሱንና የአስገደ ገ/ስላሴ ጋህዲ መጻህፍትን ያነበቡ ሁሉ አዲስ አመለካከት እንዲሚፈጥርበት አያጠራጥርም። ቢያንስ እንዲህ ብሎ መጠየቁ አይቀርም። በስልጣን ላይ ያለው ማን ነው? እውን አገር-በቀል አምባገነን ቡድን ነው? ወይስ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ለትግራይ የቆመ ዘረኛ ቡድን?

እንደኛ ፅኑ እምነት ከሆነ ኢትዮጵያ አገራችን ዛሬ የገጠማት ቅጥረኛ ጠላት (mercenary) በታሪክዋ አቻ ያልተገኘለት ነው። ያሁኑ ጠላት ድል ካደረገች ሌላ ህልውናዋን የሚፈታተን ጠላት በቀላሉ ድል ልታደርግ ትችላለች ብለን እናምናለን። ስልጣን ከጨበጠ እነሆ 19 አመት ገደማ ያስቆጠረው ጠላት ዛሬ በመላው አገሪቱ እያደረሰው ያለው ግፍና መከራ መጀመርያ እንደ ላቦራቶሪ የተጠቀመበት ቢኖር በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ የኖረውን የትግራይን ህዝብ በጦርነት፣ በረሃብና በስደት፣ በእስራትና በሞት ለአመታት ገላጋይ ባልተገኘለት መንገድ ቀጥቅጦ ካዳከሙት በኋላ ነው።

ለምሳሌ - ይላል ዛሬ በምስራቅ አውስትራልያ የፐርዝ ከተማ ኗሪ የሆነው ገ/መድህን አርአያ - ሀውዜን በደርግ የአየር ድብደባ እንድትታረድ እቅድ ያወጡት ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ ናቸው።

ለማስታወስ ያክል በአጭሩ እንዲህ ሲል ተደምጧል፤

ጊዜው ወያኔ አባላቱን በብዛት በኤርትራ እና በትግራይ እየተካሄደ በነበረው ጦርነት እየማገደ ያስጨረሰበት፣ ሌላው አባል ደግሞ መሮት ወደ ጎረቤት አገር የሚጠፋበት፤ በዚሁ ምክንያትም ወያኔ እየተመናመነ የመጣበት ጊዜ ነበር። የሻእብያ ኩሊ ሆኖ እንዲያገለግል በታማኝነት እየመሩት የነበሩት ስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ ደግሞ ድርጅቱን በትግራይ ወጣት እንደገና የሚጠናከርበት ዘዴ ዘየዱ።

ፍቱን መፍትሄ ሆኖ ያገኙት ደግሞ አንዷን የትግራይ ከተማ ከነገበያተኛው አስደምስሶ የወያኔ ፕሮፓጋንዳ አልቀበል ያለውን ወጣት ወዶ ሳይሆን ተግዶ፣ ጠመንጃ አንስቶ ደርግን ይዋጋል የሚል ነበር። ለዚህ አረመኔያዊ ተግባር ደግሞ ዕጩ ሆና ያገኟዋት ሀውዜን ነበረች።

ሀውዜን ከተማን በገበያ ቀን አስደምስሶ እልቂቱን በቪድዮ ቀድቶ በመላው አለም ማሰራጨት የሚል፤ ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ የተወሰኑ ወያኔዎች ወደ ሱዳን ተልከው ቪድዮ አነሳስ እንዲሰለጥኑ ተደረገ። ከነዚሁ ውስጥ፣ ይላል ገብረመድህን፤ ወዲ ፎቶ ሱራፌል (መቀሌ) እና ዘፋኙ እያሱ በርሄ ይገኙበታል።

ድራማው ተጀመረ። በገበያዋ ድምቀት የምትታወቀው ሀውዜን ለእርድ እንደተዘጋጀች በግ ሆኖ ምንም ሳታውቅ ኑሮዋን እንደወትሮው ለማሸነፍ ደፋ ቀና ትላለች። በሌላ በኩል ደግሞ በዋዜማው ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ ወያኔዎች ወደ ከተማዋ ገባ መልሰው ወጣ ይላሉ። መልእክቱ እንግዲህ ለደርግ ሲሆን፣ በሀውዜን ትልቅ የወያኔ ጉዳይ እንዳለ ለማስመሰል እና ደርግም ያለምንም ማመንታት የአየር ድብደባውን እንዲያካሄድ የታቀደ ነው። ቁጥራቸው 12 የሚደርሱ የወያኔ ባለ ቪድዮ ካሜራዎች ደግሞ ከተማዋን ቁልቁል ከሚያዩ ኮረብታዎች ጫፍ መሽገው ይጠባበቃሉ። ሰአትዋ ደርሳ፣ ሚጎቹ እና ሄሊኮፕተሮቹ ቦምባቸውን ያዘንቡ ጀመር። የስብሃት እና የመለስ ሰልጣኝ የካሜራ ሰዎች ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ሰው እና ከብቱ መለየት እስኪያቅት በደም የታጠበችውን

ህውዜን ቀድተው ሲያበቁ፣ ፊልሙን ሌሊቱን ወደሱዳን ተልኮ በሱዳን ቴሌቪዥን አማካኝነት የህውዜን መደምሰስ ለዓለም ህዝብ ታየ።

ስብሃት እና መለስ እንደተመኙት ይህን ዘግናኝ ፊልም ያየ የትግራይ ተወላጅ ሁሉ ሰራተኛ፣ ተማሪ፣ ገበሬ ወይም የሱዳን ስደተኛ ሳይል ሆ ብሎ ከያለበት ተጠራርጎ ወደ ወያኔ ጎረፈ። ወያኔ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰው ሃይል ተጠናከረ። ፊልሙን ያዩ የውጭ ድርጅቶች ደግሞ ደርግ እወነትም ፍፁም ፋሽሽታዊ መንግስት መሆኑን አምነው እሱን ለማጥፋት እየታገሉ ያሉት ገንጣይ እና አስገንጣይ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ እርዳታቸውን ለገሱ። ገብረመድህን አርአያ የህውዜን ጭፍጨፋ ዋና አቀነባባሪዎች ስብሃት ነጋ እና መለስ ዜናዊ መሆናቸውን የነገረው አብሮ አደጉ እና ዋና ጓደኛው ተከሉ ሃዋዝ ነበር። ተክሉ ሃዋዝ የመጀመርያው የወያኔ የደህንነት ሹመኛ ሲሆን፣ ባልታወቁ ሰዎች ተገድሎ መጣሉም ይታወቃል።

የህውዜን መታረድ ድርጅቱን እንዴት እንዳፋፋው የተገነዘቡት የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ደግሞ የጎንደርን ህዝብ ልብ ለመስለብ “ህሙሲት” የተባለችው ከተማ ልክ እንደ ህውዜን እንድትታረድ አደረጉ። በዚሁ በደርግ አረመኔያዊ ድርጊት ክፉኛ የተጎዳው የጎንደር ህዝብ ደግሞ ከዚህ የባሰ ምን እንዳይመጣ ብሎ በሩን በርግዶ ለወያኔ ከፈተ። የወሎ ህዝብም እንዲሁ ወያኔን ተገንጣይ ወንበዴ እያለ ሲዋጋ ከኖረ በኋላ “መርሳ” የተባለችው ህውዜንን የምታክል ከተማ አሁንም በቪድዮ ካሜራ አስተክሎ በለመደው መንገድ በደርግ ካስደበደበ በኋላ ቪድዮውን ያየ የወሎ ወጣት እንባውን እያፈሰሰ ወደ ወያኔ ይጎርፍ ጀመር።

የዛሬ የገብረመድህን ክፍል አንድ ፅሁፍ የሚያተኩረው በ 77ቱ ድርቅ የትግራይ ህዝብ በውድም ሆነ በግድ ወደ ሱዳን እንዲሰደድ ከተደረገ በኋላ በብዙ ሺ የሚቆጠር ህዝብ በረሀብ በበሽታ እና በደርግ የአየር ደብደባ እንዳለቀ፤ ከሞት ተርፎ ሱዳን የገባው በመቶ ሺ የሞቆጠር ህዝብ ደግሞ እንዴት እርዳታ ከመላው ዓለም እንደጎረፈለት፤ በስሙ የተገኘው እርዳታ ግን ህዝቡን ለማዳን ሳይሆን የዋለው እንዴት እነ መለስ ዜናዊ ለማሌሊት ምስረታ እንዳዋሉት፣ የተረፈው ደግሞ ያላንዳች ጠያቂ በሁለቱ ግለሰቦች እጅ ገብቶ እንደቀረ ያስረዳል። የገብረመድህን እውነተኛ ታሪክ ካነበቡ በኋል የሚገነዘቡት ነገር ቢኖር በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ዛሬ እየተፈፀመ ያለው ወንጀል ድርጅቱ በመጀመርያ እንደላቦራቶር የተጠቀመበት የኢትዮጵያ አካል ቢኖር ትግራይን እንደሆነ ይገነዘባሉ። የኢትዮጵያ ጠላት የትግራይ ወዳጅ ሊሆን ፈፅሞ እንደማይቻል ያስተውላሉ። ጠላት በስልጣን ላይ እያለ ምርጫ፣ ዲሞክራሲ፣ የህግ የበላይነት ወዘተ ሊሰፍን እንደማይችል በሙሉ ልብ ይተማመናሉ።

በበርካታ አገሮች ምግብ ተትረፍርፎ “ውፍረት” እንደ የጤና ጠንቅ ሆኖ በሚታይበት ዘመን፣ በጠላት ስር የወደቀው ኢትዮጵያዊው ደግሞ በቀን አንድ ጊዜ እንኳ በልቶ መዋል አቅቶት ሰብአዊና ብሄራዊ ክብሩን አጥቶ፣ ተዋርዶ የሊጋሽ ሀገሮች ተመፅዋች ሆኖ ቀርቷል። ስለዚህ ጠላት እያለ ኢትዮጵያ ከረሃብ ትላቀቃለች ማለት ዘበት መሆኑን ይተማመናሉ።

ጠላት ገነዘብ እስካገኘበት ድረስ ያገርዎ ለም መሬት ለውጭ አገር ቱጃሮች ይቸበቸባል። ኢትዮጵያዊው ደግሞ እርስ በራሱ እየተናቆረ እንዲፋለስ ይደረጋል። አገሪቱ በአንደ ግለሰብ ተቀፍድዳ የታሰረች እንጂ ህወሓት ወይም ኢህአዴግ የሚባሉ ደርጅቶች ባዶ መሆናቸውን ያውቃሉ። ሰውየው ሲጠፋ ድርጅቶቹ ደግሞ እንደ ጉም በነው እንደሚጠፉ ይረዳሉ። ደጋግመው የገደሉት እና ፀረ-ሰብ ወንጀል (Crimes against Humanity) የፈፀሙበት የትግራይ ህዝብ ደግሞ ለሱ እንደቆሙ፣ እሱም እንደደላው አርገው ያወሩለታል። ጠላት ኢትዮጵያዊው አንድ እንዳይሆን ጥላቻ እና አለመተማመን እንዲነገስ ያደረጋል። ኢትዮጵያዊው ይህ ሁሉ ተንኮል ገልጦ ሲያውቀው ጊዜ ሳያጠፋ የአንድነት እና የነፃነት ችቦ ያበራል፡፡ የድል ጎዳናም ወለል ብሎ ይታየዋል። ጠላት ሊበታትናት ያጠመዳት አገራችንም በድል አድራጊነት ነፃ ትወጣለች።

# የ77ቱ ዓ.ም ድርቅ በትግራይ

**(ክፍል አንድ)**

በ1975 ዓ.ም በከፊል ትግራይ በድርቅ ለተጎዳው ህዝብ መከፋፈል የሚገባውን እርዳታ ህ.ወ.ሓ.ት.እንደተጠቀመበት በሌላ ዝግጅት ገልጨ ነበር። በ1976 ዓ.ም በበልግና በክረምት ይጠበቅ የነበረው ዝናብ እንዳለፈው ቀረ።አመቱን ሙሉ ዝናብ ባለመጣሉ የውሃ ኩሬዎችና ወንዞች ደረቁ። በዚህ የተነሳ የቤት እንስሳት የሚበሉት ሳር እና ቅጠል ጠፋ የሚጠጡት ውሃ በማጣት በየቦታው ወድቀው ቀሩ። የድርቁ ጦስ

በእንስሳት ብቻ አላቆመም ሕጻናት፤አረጋዊያን እናቶች አባቶችን ጨምሮ ፉት የሚባል ውሃ የሚቀመስ እህል ጠፍቶ በየመንገዱና ጫካው ሬሳ ቀባሪ አቶ የጅብና የሌሎች አውሬ መጫወቻ ሆነ። ህጻናት የሞቱ እናታቸውን ጡት እየጋጡ በተራቸው አሸለቡ።ሕዝብ እንደቅጠል ረገፈ።

ሁኔታው ለአለም ሕብረተሰብ ጀሮ ደረሰ፤ በመቀጠልም የእርዳታ ጥሪ ተስተጋባ። በርካታ ጋዜጠኞችና የለጋሽ ሀገራት ተወካዮች ሁኔታውን በአካል ተገኝተው የተመለከቱት፤ ይህንኑ አሰቃቂ ክፉ ቀን ያዪ በአፋጣኝ ለአለም ሕብረተሰብ እርዳታውን እንዲቸር አልቅሰው ለምኑ ተማጸኑ፤ የአለም ሕብረተሰብም አፋጣኝ ምላሽ ሰጠ።

በዚህ ወቅት የህ.ወ.ሓ.ት. አመራር በድርቅ የተጎዳው የትግራይ ሕዝብ ወደ ሱዳን እንዲሰደድ በእዙ ስር ለሚገኘው የህዝብ ግንኙነት ትእዛዝ አስተላለፈ። በዚሁ መሰረት የቀጠና (በሪጂን) ሶስት ሀላፊ በነበረው አሸብር ንርኣዮ የበላይ መሪነት በየወረዳውና በየጣቢያው ያሉ የህዝብ ግንኙነት አባላት አማካኝነት ተግባራዊ ሆነ። አሸብር ከእኔ ጋር ኣፋር ውስጥ ወታደራዊ ትምህርት ሰልጥነን ስንጨርስ ከመጀመሪያው በሕዝብ ሥራ የተመደበ ሲሆን ቀስ ብሎ የሚናገር በታጋዩም ሆነ በሕዝቡም የሚወደድ ፀባይ ያለው ነበር። ከዚህም በተጨማሪ አሸብርን በዚሁ የስደተኛ አመላላሽነት የመደቡት ብዙው ሺህ የሚቆጠረው ስደተኛ የራያ ስደተኛ ስለነበር እሱንም ስለሚያውቁት በዚህ ለመጠቀም አስልተው የተጠቀሙበት ስልት ነበር። የህ.ወ.ሓ.ት. አመራር ስንት ሰው በስደት መፈናቀል እንዳለበትም አስቀድመው በእቅድ ይዘውታል። ስደተኛው ህዝብ ገና ጉዞ ሳይጀምር ሱዳን እንደደረሱ የሚያርፉበት ቦታዎች፤

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ. ትዋባ | 250,000 ሕዝብ፤ | |
| 2ኛ. እንጉርጃ | 500,000 ሕዝብ፤ | |
| 3ኛ.ሰፈዋ | 350,000 ሕዝብ እንዲያርፍባቸው ጣቢያወች ተመድበው | |

ቦታ ድልድል አደረጉ።

ስደተኛው ከየቦታው በውዴታም አብዛኛው ደግሞ በግዴታ ወደ ሱዳን እንዲፈልስ ተደረገ፤ በጉዞው ወቅት ያቀረቡለት ዱቄት ዘይት ስኳር ለህፃናት ወተት ወይም ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው ዝግጅት አልነበረም። በጉዞው ውሃ ጥምና ረሀብ ከሚጎዳው በተጨማሪ ጉዞው በቀን በመሆኑ የተነሳ ደርግ በሚግ 23 እና 21 እንደዚሁም በተዋጊ ሄሊኮፕተርም በታገዘ የአየር ድብደባ ብዙ ሰው ተገደለ። በመጨረሻም የሞተው ሞቶ የቀረው በ6 ሳምንት ወስጥ ሱዳን ጠቅልሎ ገባ። በየመንገዱ የሚበሉት ምግብ አልነበራቸውም። በሱዳን ፓርት ግን በየአይነቱ እህል፤ ስኳር፤ ሻይ ቅጠል፤ ለህፃናት አልሚ ምግብ ወተት ወዘተ ቀደም ብሎ የተከማቸ ነበር። በየጊዜውም ያለማቋረጥም በትልልቅ መርከቦች እየተጫኑ መራገፉ እንደቀጠለ ነበር።

የሚያሳዝነው ትግራይ ውስጥ የቀሩት በበሽታና በርሃብ ሲሞቱ በስማቸው ከተቀበሉት እርዳታ ከመስጠት ይልቅ ጋዜጠኞች እያስመጡ አጥንታቸው ላይ የደረቀ ቆዳቸውን፤ ከእናታቸው ጋር ተጣብቀው የሞቱትን ሬሳ እየመረጡና እርቃናቸውን የቀሩትን እየለዩ ፎቶግፍና ቪዲዮ በማስነሳት ለአለም ህብረተሰብ እንዲጋለጡ በማድረግና በሱዳን የስደተኛ ሰፈር መጠለያ ያጎሩአቸውም በተመሳሳይ ሁኔታ የተዳከሙትን ህፃን፤ እናት፤አዛውንት በሶስቱም የስደተኛ ሰፈር የውጭ ጋዜጠኞችና የወያኔ ታጋይ ፎቶግራፍ አንሸወችን አሰማርተው በቪዲዪ እየተቀረፀ በየሃገሩ በማስራጨት በለጋሽ ግበረሰናያት (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች /N.G.O/ አማካኝነትመለመኛ አድርገው ምግብ፤ መዳህኒት፤ የህክምና መሳሪያ፤ ልብስ በከፍተኛ ደረጃ ተመጸወቱባቸው።

ለስደተኛው ከፖርት ሱዳን ጥሬ በቆሎ በመኪናዎች እየተጫነ በሶስቱ መጠለያ ጣቢያዎች በማከማቸት ክፍፍሉ ለአባውራ ከነቤተሰቡ ለወር 20 ወይም 15 ኪሎ በቆሎ፤ አንድ ኪሎ ሰኳር፤ ግማሽ ኪሎ ጨው በራሽን መልክ ያከፋፍላሉ ።እንደዚሁም ለብቸኛ/ቤተሰብ/ ለሌለው ደግሞ 10 ኪሎ ጥሬ በቆሎ ግማሽ ኪሎ ሱኳር ሩብ ኪሎ ጨው እንዲደርሰው ተመደበ።

ሕክምናን በተመለከተ የህ.ወ.ሓ.ት በሶስቱም ጣቢያዎች ላከማቻቸው ከ1.5 ሚሊዩን ሕዝብ በላይ ዕውቀትና ችሎታ የሌላቸውን ሁለት ሁለት ግለሰቦች በየጣቢያው መድበው የወባ ክኒን አስይዘው በመላክ ስድተኛውን አላስፈላጊ የሆነ መዳህኒት በማከፋፈል ላልተፈለገ ችግር ሲዳርጉት ከአኗኗሩ የተነሳ በተላላፊ በሽታ እንዲረግፍ አደረጉ፡ በእነዚሁ ጣቢያዎች የወያኔ ድርጅትን ወክሎ በበላይነት የተመደበው አርከበ ዕቁባይ ነበር።

መጠለያ በተመለከተም የማረፊያ ቦታ ይከለል እንጂ ጣቢያዎቹ ሰማይና ምድር ብቻ ነው ያላቸው በመሆኑም ስደተኛው የቻለው በየዛፉና በየግንዱ ስር ተጠለለ በመጨረሻም የራሳቸውን መጣለያ እንዲሰሩ

በየበረሃው ተሰማርተው ቅጠል ለቅመው ሳር አጭደው ዳስ ሰርተው እንዲኖሩ ተደረገ። ለነዚሁ ስደተኞች ከአለም ህብረተሰብ በእርዳታ የተሰጡት ሶስት ሚሊዮን ድንኳኖች ውስጥ በየጣቢያዎቹ ለህክምና ተብለው አንዳንድ ድንኳኖች ለአብነት ተዘርግተው ይታያሉ። ቀሪው በህ.ወ.ሓ.ት.እጅ ገባ። ከዚህም በላይ ወፍራም ጥቁር ብላስቲክ U.N.H.C.R የሚል እንደዚሁም ሰማያዊ ፕላስቲክ በብዛት ቢመጣም የወያኔ አመረራ አንስጥም ብለው አስቀድመው በጭነት መኪና አጓጉዘው ሰወሩት።

## የመጣው እርዳታ አከፋፈል በተመለከተ

ድርቁ በመላው ኢትዮጵያ ስለነበር የሚሰጠው ደራሽ የእርዳታ ምግብ፤ ልብስ፤ መጠለያ፤ መዳህኒት የሕክምና መሳሪያ፤ የደርግ መንግሥት፤የህ.ወ.ሓ.ት እና የሻዕቢያ አመራሮች፤ በተባበሩ መንግሥታትና የግብረሰናይ ለጋሽ ድርጅቶች በጋራ በደረሱበት ስምምት እንዲከፋፈል ተደረገ፡

1ኛ.ደርግ በሚቆጣጠራቸው ከተሞችና ገጠር አካባቢዎች ሁሉ ብቻውን እንዲያከፋፍል በቀጥታም በምፅዋና በአስብ ወደቦች እየተራገፈ የመጣውን እርዳታ ለሁሉ እንዲያደርስ፤

2ኛ.ህ.ወ.ሓ.ት.እና ሻእብያ በሚቆጣጠሩአቸው ነፃ መሬት ለሚኖረው ችግረኛ ደግሞ ፓርት ሱዳን እየተራገፈ ለህዝብ እንዲያከፋፍሉ ሲወሰን፤ ከህ.ወ.ሓ.ት አመራር ውስጥ ይህንኑ ሀላፊነት የተረከቡት መለስ ዜናዊ፤ ስብሃት ነጋ፤ አባይ ፀሀዬ፤ ስዬም መስፍን፤ አርከበ እቁባይ ሲሆኑ የጽፈት ቤቱ ስራ የሚከናወነው በመለስ ዜናዊና በስብሃት ነጋ ፊርማ ሲሆን በስምምነቱም ሁለቱ በፊርማቸው ቃል ገብተው ተረከቡ። ነገር ግን ገና ፊርማው ሳይደርቅ ቃላቸውን በማጠፍ ፈረንጅን ባገሩ ሽጠን በላነው በማለት በደስታ በፈንጠዝያ ወደትግራይ ተመለሱ። ከዚህ በኃላ ማንኛው የእርዳታ አሰጣጥ ሙሉ በሙሉ በህ.ወ.ሓ.ት.ቁጥጥር ውስጥ ሆነ። በዚሁም ጊዜ ፓርት ሱዳን የተራገፈው የምግብ፤ መድህኒት፤ ልብስ፤ ለትራንስፓርት የሚያገለግሉ ተሸከርካሪዎች፤ የጭነት መኪናዎችና ፍጥኖ ድራሽ ፒካፖች መግባታቸውን ሲያረጋግጡ የትራንስፖርት ክፍል አደራጁ ሃላፊነቱንም ለዳዊት ብርሃነ ሰጡት።

### የመጣው እርዳታ

ቀደም ብሎ በፖርት ሱዳን ከተከማቸው የምግብና ሌሎች እርዳታ እቃወች በተጨማሪ ቅባት ዘይት፤ ቅቤ፤ መዳህኒት የህክምና መሳሪያዎች በየቀኑ ሁለት የጭነት መረከቦች መጉርፍ ጀመረ። ፓርቱ እየጠበበ ስለሄደም አዳዲስ ትላልቅ ማርቸዲስ የጭነት መኪናዎች 250፤ላንድ ከሩዘር ቶዮታ 89 ቤንዚን 5,000,000 ሚሊዮን፤ ናፍጣ 4,000,000 ሚሊዮን በርሚል ደረሰ።

ከዚሁም አብሮ አካፋ ዶማ የተለያዩ መሬት መቆፈሪያ መሳሪያወች አብረው መጡ። ካለምንም ማቋረጥ የምግብ፤ ቅባት መዳህኒት የወባ ትንኝ መከላከያ አጎበሮች እና ልብስ ከመስከረም 1977 ዓ.ም እስከ አመቱ መጨረሻ ቀጠለ።በእርዳታ የተገኘው በብዛቱና መጠኑ ሲሰላ ጠቅላላ የትግራይን ክፍለ ሃገር ከተማና ገጠር ጨምሮ ለአራት ሚሊዮን ሕዝብ ካለምንም ችግር ሁለት አመት ሙሉ ሊቀልብ የሚችል እርዳታ ተገኝቷል።

ወያኔ ከደርግ በተለያየ ጊዜ የነጠቃቻው 80 የጭነት መኪናዎች እና ለእርዳታ የተላኩ 250 የጭነት ማርቼዲስ ተጨምረው በጠቅላላ 330 የጭነት መኪናዎች ፓርቱን ስለአጣበቡት ከሱዳን መንግስት ቶሎ አነሱ የሚል ግፊት ስለመጣ መኪናዎች ከፓርት ሱዳን እየተጨኑ ገዳሪፍ መራገፍ ጀመሩ። ለዚህ ሥራ ደግሞ በዋና ሃላፊነት የተመደቡ ቀኛዝማች አስገዶም የሚባሉ የአክሱም አየር ማረፊያ ዋና ስራ ስኪያጅ የነበሩና ደርግን ከድተው ከወያኔ የተቀላቀሉ የአደዋ ሰው ነበሩ።

በዚህ አይነት የመጣውን እርዳታ በሀላፊነት የተረከቡት የህ.ወሓ.ት ማእከላዊ ኮሜቴ አባላት በስዩም መስፍን የበላይ አዛዥነት፤

1. አባዲ ዘሙ
2. ብርሃነ ገ/ክርስቶስ
3. ቴድሮስ ሓጎስ
4. የማነ ኪዳኔ እንዲቆጣጠሩ ተደረገ።

ወያኔወች ያሰደዱትንም ሆነ በትግራይ ውስጥ ለቀረው ህዝብ ከሚመጣው እህል የሚሰጠው ነገር የለም። በሱዳን ስደት ያለው መጀመሪያ እንደገለጽኩት ጥሬ በቀሎ እንደሚሰጠው ሳትረሱ በትግራይ ውስጥ የህ.ወ.ሓ.ት መሪዎች በየቁኑ በአይናቸው የሰው ሬሳ በየመንገዱ ወድቆ ፤ የሰው ልጅ በአጥንቱ ብቻ ቀርቶ እየተመለከቱትና

ህበረተሰብ እንደ ቅጥል እየረገፈ፤ የቤት እንስሳት ማለቁን ቆመው እየታዘቡ ከዚያ ሁሉ የሚጎርፍ  የእርዳታ ምግብ ሩብ ኪሎም ለችግረኛው ህዝብ አልሰጡም ይህንኑም በውስጡ ያለነው ታጋዮች በሚገባ እናውቃለን። የህ.ወ.ሓ.ት አመራር ጨካኝ፤ አረመኔ ፀረ- ህዝብ መሆኑአንዱ የሚያረጋግጠው በእሱ ስም ለምነው ያገኙትን ቀምተው በቸነፈር እንዲያልቅ የፈረዱ አረመኔዎች መሆናቸው ነው።

ይህ ወቅት የድርቅ ብቻ ሳይሆን የማ.ሌ.ሊ.ት ምስረት ጊዜም እየደረሰ ነበር። በመሆኑም በመከረም ወር 1977 ዓ.ም ፖርት ሱዳን የገባውን የስንዴ ዱቂት፤ ዘይት፤ ልብስ፤ መዳህኒት ወደ ገዳሪፍ ከተጓጓዘ በኃላ እንደገና በ12 የጭነት መኪናዎች በፈረቃ  የማ.ሌ.ሊ.ት ካድሬ ስልጠና ወደሚሰጥበት ቦታ እንዲከማች ተደረገ። የእርዳታው ንብረት ሁሉ ለዚሁ ስልጠና ወጭ መሸፈኛ ሆነ። ስልጠናውም ከ1ኛው እስከ 5ኛው ዙር የሁለት ወራት 6ኛ እና 7ኛ በሶስት ወራት ስልጠና ተከናወነ። የመጀመሪያው ሰልጣኞች መካከል መለስ ዜናዊ፤ አባይ ፀሃዬ፤ አለምስገድ ገበረ አምላክ የሰለጥኑ ሲሆን ከ1ኛ_5ኛ ዙር በተከታታይ 400 ካድሬዎች በጠቅላላ 2000ሺ.ህ ካድሬዎች ሲሰለጥኑ፤ ስልጠናው በፈንጠዝያ ማታ ማታ ጭፈራ ምግብ እንደልብ የነበረበት በየሁለት ሳምንቱ ጠላ እየተጠመቀ እነርሱ ሲሰከሩ በተቃራኒው የአካባቢው ነዋሪዎችም ህ.ወ.ሓ.ት. ምን እንደሚሰራ ትዝብት ብቻ ሳይሆን ሕዝብ በረሀብና በበሽታ እያለቀ እነሱ ለህዝብ ተብሎ በመጣው እርዳታ እየጠገቡ እየበሉ ከዚያም አልፎ እየሰከሩ መሆኑን በየቦታው ቢጀምርም ሰሚ አልነበረውም።

6ኛው ዙር እኔን፤ አዲሱ ለገሰንና ታምራት ላይኔን ጨምሮ 350 ታጋይ ሰለጠን፤በሰልጠና ወቅት በነበርንበት ሶስት ወራት ውስጥ በየሳምንቱ ሁለት በሬ ከወልቃይት እየተገዛ ይታረዳል። ጥዋት ቁርስ የፈለገ እንጀራ በወጥ ወይም አምባሻ፤ ወተት፤ ሻይ፤ እየቀረበልን ተምረን ጨረስን።

7ኛው ዙር ሰልጣኞች ሁለት ወር ትምህርታቸውን እንደተከታተሉ የማሌ.ሊ.ት ምስረታ ስለደረሰ ቀረውን ትምህርት ጉባኤው አጠገብ እንዲጨርሱ ተደረገ። ይህን ሁሉ የገለጽኩት የትግራይ ህዝብ በረሃብ እያለቀ ወያኔ ግን ለራሱ እርዳታውን የተጠቀመበት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲረዳው በተጨማሪ ያቀረብኩት መረጃ መሆኑን ለማሳየት ነው።

በሌላው ወገን ደግሞ ደርግ በያዛቸው ጣቢያዎች እህሉ ከሞላ ጎደል ይከፋፈል ስለነበር ወሬም ወያኔ በሚቆጣጠርባቸው አካባቢዎች ስለደረሰ ህዝቡ ወደ ደርግ ይዞታ  መጓዝ ሲጀምር የወያኔ አመራርም ይህን ስለአወቀ በሽሬ፤ በራያና አዘቦ ግራና ቀኝ ማንም ሰው ወደ ደርግ እንዳይገባ ትእዛዝ ስለአስተላለፉ ረሀብተኞቹ ወደ መጡበት እንዲመለሱ በኬላ ጠባቂ አማካኝነት ለማገድ ቢሞክሩም ሕዝቡ እቢ በማለቱና ጠባቂወቹም የአካባቢ ሚሊሽያ በመሆናቸው የህብረተሰቡን ችግር በሚገባ ስለተረዱ መንገዱን ከፍት በማድረግ የፈለገው ሁሉ ወደ ደርግ ገባ ተባበሩ። እርዳታውን እንዳገኙም ብዙወቹም ወደ  ወያኔ ዳግመኛ ሳይመለሱ ቀሩ።

ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ በትግራይ ህብረተሰብ ላይ የወረደ የድርቅ መቅሰፍት ቀላል  መስሎ ሊሰማው ይችል ይሆናል፡ ነገር ግን የታየው ሁኔታ ግን እጅግ  አስደንጋጭና መጥፎ ነበር። እናት ሁለት ህፃናት አቅፋ ልጆቿና እሷ  ሙተው የታዩበት በተለያዩ  ህፃን እናቱ ሞታ ሬሳ እየጠባ የታየበት፤አዛውንቶች በጅብ ተበልተው የጅብ ትራፊ በየበረሃው የወደቀበት፤አክሱም፤ ሽሬ፤ ኢጋማ፤እንደርታ፤ ራያና አዘቦ፤ አድዋ፤ ተምቤን፤ ክለተ አውላሎ፤ እስከ ራያና ቆቦ በተለያዩ ጊዜያት እና በተዳጋጋሚ የእርዳታ ለጋሾች እየተዘዋወሩ ተመልክተው የእርዳታ አስፈላጊነቱን ምስክርነት ለአለም የሰጡበትና አለምን ተማጽነው ያገኙትን እርዳታ ሕዝቡ ሳይጠቀም ወያኔ የፖለቲካ ትርፍ  ያካበተበት ብቻ ሳይሆን ሀብት ያግበሰበሰበት አጋጣሚ ነው።የወያኔ ከሃዲና አረመኔ አመራር የፈፀመው ተግባር እንኳን ቆሜልሀለሁ ከሚል ድርጅት ይቅርና የሰው ፍጡር አስተሳሰብ ካለው የማይጠበቅ እኩይ ተግባር ነው።

ይህን ከዚህ ላይ ልግታውና  ወደ ሱዳን የገባው ስደተኛ የሚሰጠውን እርዳታ በተመለከተ በድርቅ የተጎዳው ሕዝብ የተለገሰው መጠን ሰፊ እርዳታ አመራሩ ምን ሥራ ቀጠለበት? ከላይ እንደገለጽኩት ደግሞ የማሌሊት ምስረታ ማግስት ስለነበር በቅድሚያ የማሌሊት ምስረታን ሁኔታ እመለከታለሁ። ይህኑ በክፍል ሁለት ይዥላችሁ እቀርባለሁ።

(TPLF is a mercenary-controlled group that cannot be reformed. Like apartheid, it should be dismantled.)